


በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

# የምስጋና መለኮታዊ ስጦታ

## ምስጋና ያለው ልብ የሚመጣው ለሰማይ አባታችን ለበረከቶቹ እና በአካባቢያችን ለሚገኙትም በህይወታችን ለሚያመጡት ነገሮች ሁሉ ምስጋናን በመግለፅ ነው።

ይህ አስደናቂ ጉባኤ ነበር። እንደ ቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት በተመደብኩበት ጊዜ፣ “አንድ ሀላፊነት ለእራሴ እወስዳለሁ። የታበርናክል ዘማሪዎች አማካሪ እሆናለሁ” አልኩኝ። በዘማሪዎቹ ታላቅ ኩራት ይሰማኛል!

እናቴ አንድ ጊዜ እንዲህ አለችኝ፣ “ቶሚ፣ ስላደረካቸው በሙሉ ታላቅ ኩራት ይሰማኛል። ነገር ግን የምንግርህ አንድ ነገር አለ። ፒያኖ መጫወትህን መቀጠል ነበረብህ።”

ስለዚህ ወደ ፒያኖው ሄድኩኝና አንድ ዘፈን ተጫወትኩላት፤ “እንሂድ፣ እንሂድ፣ ወደ ልደት ፓርቲ።”[1] ከዛም ራሷን ሳምኳት፣ እርሷም አቀፈችኝ።

ስለእርሷ አስባለሁ። ስለአባቴም አስባለሁ። በእኔ ላይ ተፅዕኖ ስለነበራቸው አጠቃላይ ባለስልጣኖችም እና ሌሎች፣ በተጨማሪም ለምድጃቸው ዶሮዎች፣ አንዳንዴም ፤ለኪሳቸው ትንሽ ገንዘብ በመያዝ እጎበኛቸው የነበሩ መበለቶችንም አስብባቸዋለሁ—እነርሱም 85 ነበሩ— ።

አንድ ምሽት አንዷን ጎበኘሁ። ለሊት ነበር፣ እናም ወደ መንከባከቢያ ቤት ሄድኩኝ፣ እናም ተቀባይዋም እንዲህ አለች፣ “ሳይተኙ አይቀሩም፣ ነገር ግን ‘እንደሚመጣ አውቃለሁ ’በማለት እንድቀሰቅሳቸው ጠይቀውኛል።’”

እጃቸውን ያዝኩኝ፣ እናም ስሜን ጠሩኝ። ተነስተው ነበር። እጆቼን ሳመቸ እናም “እንደምትመጣ አውቄ ነበር” አሉኝ። እንዴት አልመጣም ነበር?

አስደሳች ሙዚቃ እንደዚህ ይነካኛል።

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ የእውነት፣ የተስፋ፣ እና የፍቅር የሚያነሳሱ መልእክቶችን ሰምተናል። ለኃጢያታችን ወደከፈለው፣ የምንኖርበትን መንገድ እና እንዴት እንደምንጸልይ ያሳየን፣ እና በስራው የአገልግሎትን በረከቶች ወደሳየን ወደአደኛችን እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሀሳቦቻችን ዞረዋል።

በመፅሐፈ ሉቃስ፣ ምዕራፍ 17 ውስጥ ስለእርስ እናነባለን፤

“ወደ ኢየሩሳሌምም ሲሄድ በገሊላና በሰማርያ መካከል አለፈ።

“ወደ አንዲት መንደርም ሲገባ በሩቅ የቆሙት አሥር ለምጻሞች ተገናኙት፤

“እነርሱም እየጮኹ። ኢየሱስ ሆይ፥ አቤቱ፥ ማረን አሉ።

“አይቶም። ሂዱ፥ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ አላቸው። እነሆም፥ ሲሄዱ ነጹ።

“ከእነርሱም አንዱ እንደ ተፈወሰ ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፥

“እያመሰገነውም በእግሩ ፊት በግንባሩ ወደቀ፤ እርሱም ሳምራዊ ነበረ።

“ኢየሱስም መልሶ። አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ?

“ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም አለ።

“እርሱንም፣ ተነሣና ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።”[2]

በመለኮታዊ አማላጅነት፣ ለምጻም የነበሩት ክፉ እና ማለቂያ ከሌለው ሞት ድነው፣ አዲስ ህይወት ተሰጥቷቸው ነበር። አንዱ ለመምህር ላሳየው ምስጋና በረከትን አገኘ፣ የቀሩት ዘጠኞች ምስጋና አለመኖርም አሳዝኖታል።

ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ለምንቀበለው በረከቶች ምስጋና ለመስጠት እናስታውሳለን? ልባዊ ምስጋና መስጠት በረከቶቻችንን እንድናውቃቸው እንዲረዳን ብቻ ሳይሆን የሰማይ በሮች እንዲከፈቱና የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲሰማን ይረዳናል።

ፕሬዘደንት ሒንክሊ እንዳሉት፤ “በምስጋና ስትሄዱ፣ በትንቢት እና ሀሳብ እና በኩራት አትሄዱም፤ ለእናንተ ብቁ በሆነው እና በህይወታችሁ በሚባርካችሁ በምስጋና መንፈስ እየሄዳችሁ ናችሁ።”[3]

በማቴዎስ ውስጥ ሌላ የምስጋና ታሪክ አለን፣ በዚህም ጊዜ ይህም የሚገለጸው በአዳኝ ነበር። ለሶስት ቀናት በምድረበዳ ውስጥ ሲጓዝ፣ ከ4000 በላይ ህዝቦች ተከተሉት እና ከእርሱም ጋር ተጓዙ። በሶስቱ ቀናት ውስጥ ምንም ምግብ ስላልበሉ ለእነሱም ርህራሄ ተሰማው። ደቀመዛሙርቱም፣ “ይህን ያህል ሕዝብ የሚያጠግብ ይህን ያህል እንጀራ በምድረበዳ ከወዴት እናገኛለን?” ብለው ጠየቁ። እንደብዙዎቻችን የተመለከቱት ያልነበረውን ነገር ብቻ ነበር።

“ኢየሱስም። ስንት እንጀራ አላችሁ? አላቸው። [ደቀመዛሙርቱም]፣ ሰባት፥ ጥቂትም ትንሽ ዓሣ አሉት።

“ሕዝቡም በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፤

“ሰባቱንም እንጀራ ዓሣውንም ይዞ *አመሰገነ*ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ።”

አደኝ ለነበራቸው ምስጋና እንደቀረበ ተመልከቱ፣ ከዛም ታምራት ተከተለ። “ሁሉም በሉና ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቁርስራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሡ።”[4]

ሁላችንም ከበረከቶቻችን በላይ ስለሌለን ነገር ላይ እንደምናተኩር አንዳንዴም ሁላችንም አጋጥሞናል። የግሪክ ፈላሳፊው ኤፒክቲተስ  እንዳለው፣ “ለሌለው ነገሮች የማያዘን፣ ግን ባለው ነገሮች የሚደሰት ሰው ጥበበኛ ሰው ነው።”[5]

ምስጋና መለኮታዊ መመሪያ ነው። ጌታ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚስ በተገለጠው ራዕይ እንደወጀው፣

“ጌታ አምላክህን በሁሉም ነገሮች አመስግን። . . .

“በሁሉም ነገሮች ውስጥ የእርሱ እጅ እንዳለበት ከማይመሰክሩ እና ትእዛዙን ከማያከብሩ በቀር፣ በምንም ሰው እግዚአብሔርን አያስቀይመውም፣ ወይም በማንም ላይ ቁጣው አይቀጣጠልም።”[6]

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ “[እግዚአብሔር] በየቀኑ በእናንተ ላይ ባደረገው ስለበዛው ምህረቱና በረከቱ በምስጋና እንድትኖሩ” ተብለን ተነግሮናል።”[7]

ጉደዮቻችን ምንም ቢሆኑም፣ ስለበረከቶቻችን ልለጥት ቆም ብለን ብናስብባቸው፣ እያንዳንዳችን ምስጋና እንዲሰማን የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉን።

ይህም በምድር ላይ ለመሆን አስደናቂ የሆነ ጊዜ ነው። በምድር ውስጥ ትክክል ያልሆነ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፣ ጥሩ እና ትክክል የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። የሚሳኩ ጋብቻዎች፣ ልጆቻቸውን የሚወዱና ለእነርሱም መስዋዖት የሚያደርጉ ወላጆች፣ ስለእኛ የሚያስቡ እና የሚረዱን ጓደኞዎች፣ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች አሉ። ህይወቶቻችን መቆጠር በማይቻል መንገድ ተባርከዋል።

በመጥፎ አስተሳሰብ ውስጥ ለመቆየት እምቢ ስንል እና የምስጋና አስተሳሰብ በልባችን ስናሳድግ፣ እራሳችንን እና ሌሎችን ከፍ ለማድረግ እንችላለን። ምስጋና አለመስጠት ከመጥፎ ኃጢያቶች ጋር የሚቆጠር ቢሆን፣ ከዛም ምስጋና መስጠት ከስነምግባር ክብሮች መካከል ቦታውን ይወስዳል። አንድ ሰው እንዳለው ምስጋና መስጠት ታላቁ ስነምግባር ብቻ ሳይሆን የሌሎቹ ወላጅ ነው።[8]

በውስጣችን የምስጋና አስተሳሰብን ለማሳደግ እንዴት እንችላለን። ፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ መልስ ሰተዋል። እንዲህም አሉ፣ “ምስጋና የሚሰጥ ሰው በአለም ውስጥ ምስጋና የሚሰጥበት ብዙ ነገሮች ያያል፣ እናም ለእርሱም ጥሩም ከክፋው በላይ ነው። ፍቅር ቅናትን ያሸንፋል፣ ብርሀንም ከህይወቱ ጭለማን ያስወጣል።” እንዲህም ቀጠሉ፣ “ትዕቢት ምስጋናችንን ያጠፋል እናም በቦታው ራስ ወደድነትን ያስቀምጣል። ምስጋና በሚኖረው እና ደስተኛ ነፍስ ፊት መገኘት እንዴት ደስተኛ ያደርገናል፣ እናም በጸሎታዊ ህይወትን ወደ እግዚአብሔር እና ወደሰው የምስጋና አስተሳሰብን እንዴት በጥንቃቄ ማሳደግስ ይገባናል!”[9]

ፕሬዘደንት ስሚዝ ጸሎታዊ ህይወት ምስጋና ሰጪ ለመሆን ቁልፍ ነው ብለው ነግረውናል።

ንብረቶች ደስተኛ እና አመስጋኝ ያደርጉናል? ምናልባት ለትንሽ ጊዜ። ምናልባት ለጥቂት ጊዜ። ነገር ግን፣ ጥልቅ እና የሚቆይ ደስተኛነት እና አመስጋኝነት የሚሰጡን ነገሮች ገንዘብ የማይገዛቸው ቤተሰቦቻችን፣ ወንጌል፣ ጥሩ ጓደኞች፣ ጤንነታችን፣ ችሎታችን፣ እና በአካባቢያችን በሚገኙት የምንቀበለው ፍቅር ናቸው። በሚያሳዝን ሁኔታም እነዚህ ነገሮች እራሳችን ችላ እንድንላቸው የምንፈቅዳቸው ነገሮች ናቸው።

የእንግሊዝ ጸሀፊው Aldous Huxley እንደጻፈው፣ “ብዙ ሰዎች ነገሮችን ችላ ለማለት መጠን የሌለው ችሎታ አላቸው።”[10]

ምስጋናችንን ከሁሉም በላይ የሚገባቸውን ብዙ ጊዜ ችላ እንላቸዋለን። ምስጋና ለመግለፅ እስከሚያመልጠን ድረስ አንጠብቅ። ስለሞቱባት ስለምታፈቅራቸው ስትናገር፣ አንድ ሴት የሚቆጫትን እንዲህ ገለጸች፣ “እነዛን ደስተኛ ቀናት አስታውሳለሁ እናም ብዙ ጊዜም ለሙታን ጆሮዎች በህይወት ሊኖራቸው የሚገባቸውን ምስጋናን ለመንገር ለመቻል እመኛለሁ።”[11]

የምንወደቻውን ስናጣ ይህም በልባችን አንዳንድ ቁጨት ሊያመጣብን ይችላል። እነዚህን አይነት ስሜታዎች ፍቅራችንን እና ምስጋናችንን በመግለፅ በተቻለን መጠን እናስቀንሳቸው ። መቼ ይህን ለማድረግ እንደማንችል አናውቅምና።

ምስጋና ያለው ልብ የሚመጣው ለሰማይ አባታችን ለበረከቶቹ እና በአካባቢያችን ለሚገኙትም በህይወታችን ለሚያመጡት ነገሮች ሁሉ ምስጋናን በመግለፅ ነው። ይህም የምስጋና አስተሳሰብን እስከምናሳድግ ድረስ ልዩ ጥረት ያስፈልገዋል። ብዙ ጊዜ ምስጋና ይሰማናል እናም ምስጋና ለመስጠት *እናስባለን*ነገር ግን ይህን ለማድረግ እንረሳለን ወይም ሳናደርገው ጊዜ ያልፋል። አንድ ሰው እንዳለው “ምስጋና መሰማት እና ይህን አለመግለፅ ስጦታን እንደመግዛት እና አለመስጠት ነው ብለዋል።”[12]

ፈተና እና ችግሮችን በህይወታችን ውስጥ ስናገኛቸው፣ በበረከቶች ላይ ለማተኮር አስቸጋሪ ይሆንብናል። ነገር ግን፣ በጥልቅ ከተመለከትን፣ ስንት እንደተሰጠን ሊሰማን እና ልናውቀው እንችላለን።

በከባድ ችግሮች መካከል በረከቶችን ለማግኘት ስለቻሉ አንድ ቤተሰብ ታሪክ ልንገራችሁ። ይህም በነበረው መልእክት ምክንያት ከብዙ አመታት በፊት ባነበውም የጠበኩት ታሪክ ነበር። ታሪኩም በአሜሪካዊ ጋዜጣ ያሳተመው በጎርደን ግሪን የተጻፈ ነው።

ጎርደን እርሱ እና ወንድሞቹ እንደ ሌሎች ልጆች ከመጫወት ወደ ቤት በችኮላ መመለስ በነበረበት በካናዳ እርሻ ላይ ያደገ ነበር። አባታቸው ግን ስራዎቻቸው ጥቅም እንደነበራቸው እንዲያዩ ለመርዳት ችሎታ የነበረው ነበር። ይህም ከአዝመራ በኋላ በምስጋና መስጫ ቀን ከአባታቸው ጋር ያደረጉትን ነገሮች በሙሉ እንዲመለከቱ በሚያደርግበት ጊዜ ይህም በልዩ እውነት ነው። ያለውን ነገሮች ሁሉ ተመለከተ።

በምስጋና መስጫ ቀን ጠዋት፣ ፍራፍሬዎች፣ ቀይ ስር፣ ባቄላ፣ ካሮት፣ እና ድንቾች፣ እና ሌሎች የአትክልት ፍሬዎችን ለመመልከት ይወስዳቸዋል። ልጆቹ ሁሉንም ነገሮች እንዲቆጥሩ ያደርጋቸዋል። ከዛም ወደ ሳር መሰብሰቢያው ሄደው ስንት ሳሮች እንደሰበሰቡ እና ስንት እህል እንደሰበሰቡ ይቆጥራሉ። ላሞችን፣ አሳማዎችን፣

ዶሮዎችን፣ እና ሌሎች እንስሳቶችን ይቆጥራሉ። ላሞችን አሳማዎችን፣ ዶሮዎችን፣ ተርኪዎችን፣ እና ዳክዮችን ቆጠሩ። አባታቸው አቋቋማቸው እንዴት እንደሆኑ እንዲያውቁ ይፈልጋል፣ ነገር ግን በድግስ ቀን፣ እግዚአብሔር እንዴት እንደባረካቸው እና ላሳለፉት ለብዙ ስራ ስአቶች ፈገግታ እንደነበረው እንዲገባቸው ይፈልግ ነበር። በመጨረሻ እናታቸው ያዘጋጀችውን ምግብ ለመመገብ በሚቀመጡበት ጊዜ፣ በረከቶቹ በስሜታ የሚሰሟቸው ነበሩ።

ጎርደን ከሁሉም በላይ የሚያስታውሰው የምስጋና መስጫው ቀን ግን ምንም እንደሌላቸው በሚመስልበት አንድ ጊዜ የነበረውን ነው።

አመቱ በደንብ ተጀመረ፤ የቀረ ያለፈው አመት ሳር፣ ብዙ የእህል ዘሮች፣ አራት አሳማዎች ነበራቸው፣ እናም አባታቸው ሳር የሚያነሱበትን መሳሪያ ለመግዛት ትንሽ ገንዘብ አጠራቀሞ ነበር። ይህም በከተማቸው ኤሌክትሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣበት ዘመን ነበር።

በአንድ ምሽት የጎርደን እናት ልብሶችን እያጠበች እያለች፣ አባትየው ለማጠብ ተራውን ወሰደ እና እርሷም ልብስ ለመስፋት ቁጭ አለች። እንዲህም አላት፣ "ከመተኛት በላይ ልብሶችን ታጥቢያለሽ። ኤሌክትሪኩን እናስገባ?" ምንም እንኳን በሀሳቡ ብትደሰትም፣ ሳር የሚያነሳውን ማሺን ስላለመገዛቱ በማሰብ ትንሽ አለቀሰች።

በዚያም አመት ኤሌክትሪኩ ወደቤታቸው ገባ። ምንም እንኳን ድንቅ የሆነ ባይሆንም፣ በየቀኑ ልብስ የሚያጥብ ማሺን እና መብራት በቤታቸው ውስጥ ገባ። መሞላት ያለበት ፋኖስ፣ ወይም ማፅዳት የሚያስፈልጋቸው የጭስ ማውጫም አልነበረም። ፋኖሶቹ በቤቱ ጣራ ስር እንዲቀመጡ ተወሰዱ።

በዚያ አመት የነበራቸው ጥሩ ነገር በእርሻቸው ውስጥ የገባው ኤሌክትሪክ ብቻ ነበር። ተክሉ ማደግ ሲጀምር፣ ዝናብ ተጀመረ። ውሀው በመጨረሻ መድረቅ ሲጀምር፣ ምንም የቀረ አትክልት አልነበረም። እንደገናም ተከሉ፣ ነገር ግን ዝናቡ አትክልቱን እንደገና አጠፋባቸው። ድንቾቻቸው በምድር ውስጥ በሰበሱ። ከብቶቻቸውን፣ አሳማዎቻቸውን እና አንድ ሁለት ላሞቻቸውን ሁሉም ሰዎች እንደዚህ ያደርጉ ስለነበረ ብዙ ባልሆነ ዋጋ ሸጡ። በዚያ አመት የሰበሰቡት ቢኖር ከዝናቡ የተረፈው ቀይ ስር ብቻ ነበር።

ከዛም ምስጋና መስጫው ቀን እንደገና መጣ። እናታቸውም እንዲህ አለች፣ "ምናልባት በዚህ አመት ይህን አናድርግ። ዳክዬ እንኳን የለንም።"

በምስጋና መስጫ ቀን ጠዋት፣ የጎርደን አባት ጥንቸል ይዞ መጣ እና ባለቤቱን እንድትቀቅለው ጠየቃት። ይህን ያረጀ ነገር ለመቀቀል ረጅም ጊዜ ይፈጃል በማለት ያለፍላጎት መስራት ጀመረች። ከተሰበሰበው ቀይ ስር ጋር ምግቡ በጠረጴዛ ላይ ሲቀመጥ፣ ልጆቹ አንበላም አሉ። የጎርደን እናት አለቀሰች፣ ከዛም አባትየው ያልታሰበ ነገርን አደረገ። ምግብና እቃዎች ወደሚያስቀምጡበት ሄደ፣ እናም የዘይት ፋኖስን ወደጠረጴዛም አምጥቶ ማንደድ ጀመረ። ልጆቹንም የኤሌክትሪክ መብራትን እንዲያጠፉ ነገራቸው። ፋኖሱ ብቻ ሲኖርም፣ ከዚህ በፊት እንደዚህ ጭለማ እንደነበረ ለማመን አልቻሉም ነበር። ከኤሌክትሪክ ብርሀን በፊት እንዴት ምንም ነገሮችን ለማየት ችለው እንደነበር ተደነቁ።

ምግቡ ተባረከ፣ ሁሉም በሉ። እራት ካለቀ በኋላ፣ በጸጥታ ተቀመጡ። ጎርደንም እንዲህ ጻፈ፤

"በድሮው የፋኖስ ብርሀን በግልፅ ለማይት ቻልን። . . .

አስደሳች ምግብ ነበር። ጥንቸሉ እንደ ተርኪ ጣፋጭ ነበረ፣ እናም ቀይ ስሩም ከምናስታውሰው በላይ ጣፋጭ ነበር። . . .

". . . ቤታችን . . . ምንም ብናጣም ሀብታችን ነበር"።[13]

ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ምስጋና መግለፅ ለጋስነትና ተከባሪ ነው፤ ምስጋናን ማሳየት ደግነትና ልዑላዊነት ነው፤ በልባችን ውስጥ፡ሁልጊዜ በሚገኝ ምስጋና መኖር ግን ሰማይን እንደመንካት ነው።

በዚህ ጠዋት ንግግሬን ስፈፅም፣ ምስጋና ከሚሰሙን ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ በተጨማሪ፣ ለጌታችን እና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን ምስጋና ሁልጊዜም እናንጸባርቅ ዘንድ ጸሎቴ ነው። ግርማዊ ወንጌሉ ለህይወት ታላቅ ለሆኑት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፤ ከየት ነው የመጣነው? ለምን እዚህ አለን? ስንሞት ነፍሳችን የት ይሄዳል? ለሚሉት ጥያቄዎች ግርማዊው ወንጌሉ መልስ ይሰጣል። ያም ወንጌል በጭለማ ለሚኖሩት የእውነት መለኮታዊ ብርሀንን ያመጣል።

እንዴት እንደምንጸልይ አስተማረን። እንዴት እንደምንኖር አስተማረን። እንዴት መሞት እንዳለብን አስተማረን። ህይወቱ የፍቅር ውርስ ነው። በሽተኛዎችን ፈወሰ፣ የተረገገጡትን አነሳ፣ ኃጢያተኛን አዳነ።

በመጨረሻም፣ ብቻውን ቆመ። አንዳንድ ሐዋሪያት ተጠራጠሩ፤ አንድም ካደው። የሮሜ ወታደሮች ጎኑን በሱ። የተናደዱት ህዝቦችም ህይወቱን አጠፉ። ነገር ግን በጎልጎታ "አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ያላቸው የርህራሄ ቃላቱ ተደጋግመው ይሰማሉ።[14]

የሀዘን ሰው የነበረው፣ እና ከስቃይ ጋር የተዋወቀው ማን ነበር?[15] "የግርማ ንጉስ፣"[16] የጌቶች ጌታ ማን ነው? እርሱም መምህራችን ነው። አዳኛችን ነው። የእግዚአብሔር ልጅን ነው። የደህንነታችን ጸሀፊም ነው። "ተከተሉኝ" ብሎ ይጠራል።[17] "ሂዱና እንዲሁም አድርጉ" ብሎ ያስተምራል።[18] "ትእዛዛቴን ጠብቁ" ብሎም ይለምናል።[19]

እንከተለው። የእርሱን ምሳሌንም እንከተል። ቃላቱንም እናክብር። ይህንም በማድረግ፣ ለእርሱ መለኮታዊ ስጦታ የሆነውን ምስጋና እንሰጠዋለን።

ልባዊ፣ በልብ የሚሰማ ጸሎቴም በእያንዳንዳችን ህይወቶች ውስጥ ያን አስደናቂ የምስጋና ስነምግባር እንድናሳይ ነው። ይህም አሁን እና ለዘለአለም ነፍሳችንን ያጥለቅልቀው። በቅዱሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።


**ማስታወሻዎች**

1. ጆን ቶምሰን፣ "Birthday Party," *Teaching Little Fingers to Play* (1936), 8።
2. ሉቃስ 17፥11–19።
3. *Teachings of Gordon B. Hinckley* (1997), 250።
4. ማቴዎስ15፥32–38፤ አፅንኦት የተጨመረበት።
5. *The Discourses of Epictetus; with the Encheiridion and Fragments,* trans. ጆርጅ ሎንግ (1888)፣ 429።
6. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 59፥7፣ 21።
7. አልማ 34፥38።
8. Cicero, in *A New Dictionary of Quotations on Historical Principles,* sel. H. L. Mencken (1942)፣ 491።
9. ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ፣ *Gospel Doctrine,* 5th ed. (1939)፣ 263።
10. አልዶስ ሀክስሊ፣ *Themes and Variations* (1954)፣ 66።
11. ውልያም ኤች ዴቪስ፣ *The Autobiography of a Super-Tramp* (1908)፣ 4።
12. ውልያም አርተር ዋርድ፣ in Allen Klein, comp., *Change Your Life!* (2010)፣ 15።
13. Adapted from ኤች ጎርደን ግሪን፣ "The Thanksgiving I Don't Forget፣" *Reader's Digest*፣ Nov. 1956፣ 69–71።
14. ሉቃስ 23፥34።
15. ኢሳይያስ 53፥3።
16. መዝሙር 24፥8።
17. ማቴዎስ 4፥19።
18. ሉቃስ 10፥37።
19. ዮሀንስ 14፥15።

# ለጊዜአችን ትምህርቶች

የመልከጸዴቅ የክህነት ስልጣንና የሴቶች መረዳጃ ማህበር የአራተኛው እሁዶች ትምህርቶች "ለጊዜአችን ትምህርቶች" የተወከሉ ይሆናሉ። እያንዳንድ ትምህርትም በቅርብ ከነበረው የአጠቃላይ ጉባኤ አንድ ወይም ተጨማሪ ንግግሮች መምረጥ ይቻላል። የስቴክ እና የዲስትሪክት ፕሬዘደንቶች የትኛዎቹ ንግግሮች መጠቀም እንደሚገባቸው መምረጥ ይችላሉ፣ ወይም ይህን ሀላፊነት ለኤጲስ ቆጶስ እና ለቅርንጫፍ ፕሬዘደንቶች ለመስጠት ይችላሉ። የመልከጼደቅ የክህነት ስልጣን ወንድሞች እና የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች አንድ አይነት ንግግሮችን በአንድ እሁድ ቀን ማጥናታቸው አስፈላጊነትን መሪዎች ደጋግመው ማሳሰብ ይገባቸዋል።

በአራተኛው ሰንበት ትምህርት ተሳታፊዎች የቅርቡን የአጠቃላይ ጉባኤ ጋዜጣን እንዲያጠኑ እና ወደ ክፍል እንዲያመጡ ይበረታቱ።

**ከእነዚህ ንግግሮች ትምህርትን የማዘጋጃ ሀሳቦች**

ንግግሮችን ስታጠኑ እና ስታስተምሩ መንፈስ ቅዱስ ከእናንተ ጋር እንዲሆን ጸልዩ። ሌሎች መፅሀፍቾችን በመጠቀም ትምህርትን ለማዘጋጀት ሀሳብ ይመጣላችሁ ይሆናል፣ ነገር ግን የጉባኤ ንግግሮች የተፈቀደለት የትምህርት መረጃ ነው። የተመደባችሁትም በቤተክርስትያኗ የቅርብ አጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ እንደሚገኙት ሌሎችን ወንጌሉን ለመኖር እና ለመማር እንድትረዱአቸው ነው።

የክፍል አባሎች ፍላጎትን የሚያሟሉ መሰረቶችን እና ትምህርቶችን በመፈለግ ንግግሮችን አጥኑ። ደግሞም ታሪኮችን፣ የቅዱስ መጻህፍት የተጠቀሱበትን፣ እና እነዚህን እውነቶች ለማስተማር የሚረዷችሁን ቃላቶች ፈልጉ።


መሰረቶችን እና ትምህርቶችን እንዴት እንደምታስተምሩም ዘርዝራችሁ ጻፉ። በዝርዝር በጻፋችሁት ውስጥም የክፍል አባሎቻችሁን የሚረዱ ጥያቄዎችን ጨምሩ፤

- በንግግሮች ውስጥ መሰረቶችን እና ትምህርቶችን ፈልጉበት።
- ስለትርጉማቸው የሚያስቡበት።
- የተረዱትን፣ ሀሳባቸውን፣ አጋጣሚያቸውን፣ እና ምስክሮችን የሚካፈሉበት።
- እነዚህን መሰረቶች እና ትምህርቶች በህይወታቸው የሚጠቀሙበት ጥያቄዎችን ጨምሩ።

| ወሮች | ግንቦት 2010 (እ.አ.አ)—ጥቅምት 2010 (እ.አ.አ) |
|---|---|
| ህዳር 2010 (እ.አ.አ)—ሚያዝያ 2011 (እ.አ.አ) | በህዳር 2010 (እ.አ.አ) *Liahona** የታተሙ ንግግሮች |
| ግንቦት 2011—ጥቅምት 2011 | በግንቦት 2010 (እ.አ.አ) *Liahona** የታተሙ ንግግሮች |

* እነዚህ ንግግሮች (በብዙ ቋንቋዎች) በ *conference.lds.org.* ውስጥ ይገኛሉ።

© 2010 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩኤስኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/09 (እ.አ.አ)። ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/09 (እ.አ.አ)። *First Presidency Message, November 2010* (እ.አ.አ)። Amharic። 097371 506



**በፕሬዘደንት ዲየትር ኤፍ ኡክዶርፍ**
የቀደሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ

# ከነገሮች በላይ አስፈላጊ የሆነው

*ህይወት እና የእርሷ መሯሯጥና ብዙ ጭንቀቶች ደስታ እንዲሰማችሁ የሚያስቸግራችሁ ቢያደርጉት፣ ከነገሮች በላይ አስፈላጊ የሆነውላይ እንደገና ትኩረት ለመመስጠት ጥሩ ጊዜ አሁን ነው።*

ፍጥረቱን በማጥናት ስለህይወት ስንት ለመማር እንደምንችል አስደናቂ ነው። ለምሳሌ፣ ሳይንቲስቶች የዛፍን ክቦች በመምልከት ከመቶ እና እንዲሁም ከሺህ አመቶች በፊት የአየር ጠባይና የእድገት ሁኔታው እንዴት እንደነበረ ለመገመት ይችላሉ። ከዛፎች እድገት ለመማር ከምንችለው አንዱ ነገር ቢኖር ሁኔታዎች ጥሩ በሆኑበት ዘመን፣ ዛፎች በተለመደ እድገት መጠን ያድጋሉ። ነገር ግን የእድገት ጉዳዩ ጥሩ በማይሆንበት ዘመን፣ ዛፎች እድገታቸውን ይቀንሱታል እናም ለመኖር በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ ሀይላቸውን ያሳልፋሉ።

በዚህ ጊዜ አንዳንዳችሁ፣ “ይህም ጥሩ ነው፣ ግን ስለአውሮፕላን ማብረር ይህ ይም ግንኙነት አለው?” ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። እነግራችኋለሁ።

በአውሮፕላን እየበረራችሁ በሀይለኛ ንፋስ አውሮፕላኑ ሲንቀጠቀጥ ተሰምቷችሁ ታውቃላችሁ? የአውሮፕላን በንፋስ የሚንቀጠቀጥበት ዋና ምክንያት የአየር እንቅስቃሴ በድንገት መቀየር አውሮፕላኑ ወደላይ እና ወደታች እንዲወዛወዝ፣ አቅጣጫውን እንዲቀይር እና እንዲገላታ ስለሚያደርገው ነው። አውሮፕላኖች ከምትበሩበት ጊዜ ከሚያጋጥማችሁ በንፋስ መንቀጥቀጥ በላይ ለመቋቋም የተሰራ ቢሆንም፣ ይህ የሚበሩትን ያስጨንቃቸዋል።

የአውሮፕላን አብራሪዎች የአየር መንቀጥቀጥ ሲያጋጥማቸው ምን የሚያደርጉ ይመስሏችኋል? ከአየር መንቀጥቀጡ በፍጥነት ለመውጣት ስለሚያስችለው፣ ተማሪ አብራሪ በፍጥነት መሄድ ጥሩ ዘዴ ነው ብሎ ያስብ ይሆናል ነገር ግን ይህን ማድረግ ትክክል አይደለም። ባለሙያ አብራሪ በዚህ የአየር መንቀጥቀጥ አልፎ ለመሄድ የሚያስችል ብቁ የሆነ፣ የመንቀጥቀጡን መጥፎ ተፅዕኖ የሚቀንስ በፍጥነት የሚጓዙበት መጠን እንዳለ ይገባቸዋል። ብዙ ጊዜም ይህም ማለት ፍጥነትን መቀነስ ነው። ይህም አይነት መሰረታዊ መመሪያ በመንገድ ፍጥነት መቀነሻ ላይ ለመጠቀም ይቻላል።

ስለዚህ፣ አስቸጋሪ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፣ ፍጥነትን መቀነስ፣ መንገድን ማስተካከል፣ እና አስፈላጊ በሆነው ላይ ማተኮር ጥሩ ምክር ነው።

**የዚህ ዘመን ህይወት መሯሯጥ**

ይህ ቀላል ቢሆንም በጣም አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ነው። በዛፍ ወይም በንፋስ መንቀጥቀጥ አስታያየት ስንመለከተው ተገቢ አስተሳሰብ ያለው ይመስላል፣ ነገር ግን እነዚህን መሰረታዊ መመሪያዎች በህይወታችን ላይ ለመጠቀም በሚታሰብበት ጊዜ ይህን ትምህርት ቸላ ማለቱ እንዴት ቀላል እንደሆነ ያስደንቃል። ጭንቀት ከፍ ሲል፣ ችግር ሲመጣ፣ አሳዛኝ አደጋ ሲደርስ፣ በፍጥነት ከተሯሯጥን፣ የተሻለን እንሆናለን ብሎ በማሰብ፣ ብዙ ጊዜ በመሯሯጥ እንቀጥላለን ወይም ፍጥነትን እንጨምራለን።

የእዚህ ዘመን አንድ ጸባይ ቢኖር ምንም እንኳን ችግር ወይም መደናቀፊያ ቢኖርም ፍጥነት በሚጨምር ሁኔታ እየተሯሯጥን ነን።

እውነትኛ እንሁን፤ በስራ መጠመድ ቀላል ነው። ጊዜአችንን የሚያጥለቀልቅ የስራ ዝርዝርን ሁላችንም ለማሰብ እንችላለን። አንዳንድም የእራሳቸው ዋጋ መደረግ በሚያስፈልጋቸው ዝርዝሮች ረጅምነት ይመዘናል ብለው ያስባሉ። በጭንቀትና በሚያደክም ጊዜም፣ ጊዜዎቻቸውን በስብሰባና በማይረባ ዝርዝር ያጥለቀልቃሉ። አስፈላጊ ባልሆነ ሁኔታ ህይወታቸውን ስለሚያወሳስቡ፣ ተጨማሪ ንዴት፣ የሚቀንስ ደስታ፣ እናም ህይወታቸው ትርጉም እንደሌለው ይሰማቸዋል።

ማንኛውም ምግባረ ጥሩነት ከመጠን በላይ ሲደረግ መጥፎ ልምድ ይሆናል ይባላል። ቀኖቻችንን ከመጠን በላይ በቀጠሮ መሙላት ለዚህ አስተያየት ብቁ ነው። አላማ የወፍጮ ድንጋይ እና ምኞት በአንገታችን ላይ የተጫነ ሸከም የሚሆኑበት ጊዜ ይመጣል።

**መፍትሄው ምንድን ነው?**

ጥበብ ያለው የዛፍ ክቦችን እና የአየር መንቀጥቀጥን ትምህርት ያስተውላል እናም ይጠቀምበታል።

በየቀኑ በህይወት መሯሯጥ ለመያያዝ ያለውን ፈተና ይቋቋማሉ። “ፍጥነቱን ከመጨመር በላይ ለዚህ ህይወት ብዙ አለው” የሚለውን ምክርም ይከተላሉ።[1] በአጭርም፣ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ በሆነው ላይ ያተኩራሉ።

ካህን ዳለን ኤች ኦክስ በቅርብ አጠቃላይ ጉባኤ እንዳስተማሩት፣ “ከእነዚያ የሚበልጡ ሌሎች ነገሮችን ለመምረጥ አንዳንድ ጥሩ የሆኑ ነገሮችን ማለፍ አለብን ምክንያቱም እነዚህ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነትን ያሳድጋሉ እናም ቤተሰቦችን ያጠናክራሉ።”[2]

ጥሩ ነገርን መፈለግ መሰረታዊ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መሰረታዊ መመሪያዎች ይመራል፣ እነዚህም በሚያስብ፣ ዘለአለማዊ፣ እና ሁሉን በሚያውቅ የሰማይ አባት የተገለጸ ቀላል እና ወብታዊ እውነቶች ናቸው። እነዚህ ዋና ትምህርቶችና መሰረታዊ መመሪያዎች፣ ትንሽ ልጆች እንዲገባቸው ያህል ቀላል ቢሆኑም፣ ለህይወት አስቸጋሪ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ።

ግልፅ ያልሆኑ መፍትሄዎች በምንፈልግበት ጊዜ የእነዚህን ወብትና ግልፅነት ለመመልከት ያስቸግረናል።

ለምሳሌ፣ አስትሮኗትና ኮስሞናት በምድር ምህዋር ላይ ከደረሱ በኋላ እስክሪብቶዎች በህዋ እንደማይሰሩ ለማወቅ ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም። ለዚህ ችግር መፍትሄ ለማግኘት ብዙ ብልህ ሰዎች ስራቸውን ጀመሩ። ብዙ ሺህ ሰዓቶችና ብዙ ሚልዮን ዶላሮች ፈጀ፣ ነገር ግን በመጨረሻ፣ የትም ቢሆን፣ በማንኛውም ሙቀት ልቀት፣ እና በማንኛውም ንጣፍ ላይ ለመጻፍ የሚችል እስክሪብቶ ሰሩ። ነገር ግን ለዚህ ችግር መፍትሄ እስከሚገኝ ድረስ አስትሮኗትና ኮስሞናት ምን አደረጉ። በእርሳስ ተጠቀሙ።

ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ “ቀላልነት ከሁሉም በላይ የሆነ ስልጣኔ ነው።”[3] የደስታ አላማ መሰረታዊ መመሪያን የሆነውን የደህንነት እቅድ ስንመለከት፣ በዚህ ግልጽነት የሰማይ አባታችንን ጥበብ ወብት ለመመልከት እንችላለን። ከእዚያም መንገዶችንን ወደ እርሱ መንገድ መቀየር የጥበባችን መጀመሪያ ይሆናል።

## የመሰረታዊ ሀይል

ታዋቂ የእግር ኳስ አሰልጣኝ ስልጣኔን በሚጀምሩበት በመጀመሪያው ቀን ሁልጊዜም የሚያደርገው ነገር ነበር የሚል ታሪክ አለ። የሚጫወቱበትን ኳስ አንስቶ፣ ለብዙ አመቶች ይጫወቱ ለነበሩት በማሳየት፣ “ክቡሮች፣ . . . ይህ የእግር ኳስ ነው!” ስለዚህ መጠን እና ቀርጾ፣ እንዴት በእግር እንደሚመታ፣ እንደሚያዝና፣ ከአንድ ወደሌላ እንዲሚመላለስ ይናገራል። ከእዚያም ቡድኑን ወደ ሜዳው ይወስድና፣ “ይህ የእግር ኳስ ሜዳ ነው” ይላቸዋል። በሜዳው አብረው እየሄዱ መለኪያውን፣ ቀርጹን፣ የጨዋታ ህግን፣ እና እንዴት እንደሚጫወቱ ይገልጽላቸዋል።[4]

ይህ አሰልጣን ምንም እንኳን አጋጣሚ የነበራቸው ተጫዋቾች፣ በእርግጥም ቡድኑ፣ ታላቅ የሚሆኑት መሰረታዊ የሆኑትን በማወቅ እንደሆነ አውቋል። በብልጥ ጨዋታዎችን በመለማመድ ሊሰለጥኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን የጨዋታውን መሰረት እስከሚያውቁት ድረስ፣ አሸናፊ ቡድን ለመሆን አይችሉም።

ብዙዎቻችን መሰረታዊ መመሪያዎች እንዴት አስፈላጊ እንደሆኑ ይገባናል። በሚያጓጉ ብዙ ነገሮች ግን ትኩረታችንን እናጣለን።

የታተሙ ነገሮች፣ የማስተላለፊያ ምንጮች፣ ምንም እንኳን በትክክል ከተጠቀምንባቸው እርዳታ የሚሰጡ በኤልክትሪክ የሚሰሩ መሳሪያዎች የሚጎዱ ትኩረት የሚያሳጡ ወይም የሚያለያዩ ልበ ቢስ ቦታዎች ለመሆን ይችላሉ።

በድምጾችና በምርጫዎች መካከል፣ የጋለሊ ትሁት ሰው እጆቹን ዘርግቶ ይጠብቃል። መልእክቱም ፡ “ኑ፣ ተከተሉኝ” ነው።[5] የሚናገረውም በጎላ ድምፅ ሳይሆን፣ በለስላሳ፣ ትንሽ ድምፅ ነው።[6] ከሁሉም ቦታዎች በሚያጥለቀልቁን መዝገቦች መካከል የወንጌሉ መሰረታዊ መልእክት ሊጠፋ ይችላል።

ቅዱስ መጻህፍቶች እና ህያው ነቢያት የተናገሩት ቃል ለወንጌሉ መሰረታዊ መመሪያዎችና ትምህርቶች ጥብቀት ይሰጣሉ። ወደ እነዚህ መሰረታዊ መመሪያዎች፣ ወደ ንጹህ ትምህርት፣ የምንመለሰው ታላቅ ትርጉም ወደላቸው እውነቶች የምንመለስበት ናቸውና። እና ሊገባን በጣም አስቸጋሪ ወደሚሆነው ከፍተኛ አስፈላጊነት ላለው አጋጣሚም በር ይከፍትልናል። እነዚህ ያልተወሳሰቡ መሰረታዊ መመሪያዎች ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር በስምምነት ለመኖር አስፈላጊ ናቸው። እነዚህም የሰማይ መስኮቶችን ለመክፈት አስፈላጊ ናቸው። የሰማይ አባት ለሚሰሙትና ታዛዥ ለሚሆኑት ልጆቹ ቃል እንደገባም፣ እነዚህ ወደ ሰላም፣ ደስታ፣ እና ማስተዋል ይመሩናል።

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ፍጥነታችንን መቀነሱ ጥሩ ነው፣ ለጉዳያችን በሆነው ፍጥነት እንሂድ፣ አስፈላጊ በሆነው ላይ እናተኩር፣ አይኖቻችንን ከፍ እናድርግ፣ እና ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በእውነትም እንመልከት። የሰማይ አባታችን ለልጆቹ ሙሉና ፍሬ ያለው ስጋዊ ህይወት ከዘለአለማዊ ደስታ ቃል ኪዳን ጋር ለመመስረት የሰጠውን መሰረታዊ አስተያየትንም እናስብባቸው። እኛንም “እነዚህ ነገሮች ሁሉ በጥበብና በዕቅድ [እንድናደርግ]፣ [እኛ ከአቅማችን] በላይ ፈጥኖ መሮጡ አስፈላጊ አይደለምና። [ነገር ግን] እንደገና፣ ሽልማቱን [እናሸንፍ] ዘንድ ትጉህ መሆኑ ጠቃሚ ነው” ብለው ያስተምሩናል።[7]

ወንድሞችና እህቶች፣ በትጋት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የሆኑትን ማድረግ ወደ አለም አዳኝ ይመሩናል። ለዚህም “ስለክርስቶስ እንናገራለን፣ በክርስቶስ እንደሰታለን፣ ስለክርስቶስ እንሰብካለን፣ ስለክርስቶስ ትንቢት እንናገራለን፣ እናም በትንቢታችን መሰረት እንፅፋለን።”[8] በዚህ ዘመን ብጥበጣ መምታታት፣ እና መሯሯጥ ውስጥ፣ ይህ “ከሁሉም በጣም ጥሩ የሆነ መንገድ” ነው።[9]

## መሰረታዊዎቹ ምንድን ናቸው?

ወደ ሰማይ አባታችን ስንመለስ እና ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ስለሆነም በሚመለከት የእርሱን ጥበብ ስንፈልግ፣ በተደጋጋሚ ከእግዚአብሔር ጋር፣ ከቤተሰቦቻችን ጋር፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር፣ እናም ከራሳችን ጋር ስላሉን ስለአራቱ ዋና ግንኙነቶች አስፈላጊነት እንማራለን። ህይወታችንን በፈቃደኛ አዕምሮአችን ደግመን ስንመለከተው፣ ከሁሉም በላይ ጥሩ ከሆነው መንገድ የት እንደተጠማዘዝን እናያለን። የመረዳት አይኖቻችን ይከፈታሉ፣ እናም ልባችንን ለማፅዳት እና ህይወታችንን ለማስተኮር ምን መደረግ እንዳለብን እናውቃለን።

መጀመሪያ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ቅዱስ እና አስፈላጊ ነው። የእርሱ የመንፈስ ልጆች ነን። እርሱም አባታችን ነው። ደስታችንን ይፈልጋል። እርሱን ስንፈልግ፣ ስለልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ስንማር፣ ለመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ ልባችንን ስንከፍት፣ ህይወታችን የረጋና

የማይረበሽ ይሆናል። በእግዚአብሔር ዘለአለማዊ እቅድ መሰረት ለመኖር እና ትእዛዛቱን ለማክበር ስንሞክር፣ ታላቅ ሰላም፣ ደስታና፣ መሟላትም ያጋጥመናል።

ስለእርሱ በመማር፣ ከእርሱ ጋር በመነጋገር፣ ለኃጢያቶቻችን ንስሀ መግባት፣ እና "ያለ ክርስቶስ ማንም ወደ አብ ለመምጣት" ስለማይችል ኢየሱስ ክርስቶስን በተሳታፊነት በመከተል ከሰማይ አባታችን ጋር ያለንን ግንኙነት እናሻሽላለን።[10] ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጠናከር፣ ከእርሱ ጋር ትርጉም ያለው ጊዜ ከእርሱ ጋር ሊኖረን ይገባል። በጸጥታ የየቀኑን የግለሰብ ጸሎታችንንና የቅዱስ መጻህፍት ጥናታችንን በማተኮር፣ ሁልጊዜም ሁን ለመጠቀም የምንችልበት የቤተመቅደስ መግቢያ ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ለመሆን አላማ በመስራት፣ እነዚህም ወደ ሰማይ አባታችን ለመቅረብ ጊዜአችንን እና ጥረቶቻችንን በጥበብ የምንሰጥባቸው ናቸው። የመዝሙርን ጋብዣ እናድምጥ፤ "ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ።"[11]

ሁለተኛው አስፈላጊ ግንኙነታችን ከቤተሰቦቻችን ጋር ነው። "ማንኛውም አይነት ውጤታማነት በቤት ውስጥ መውደቅን የሚያስተካከል የለም" ስለሚባል[12] በዚህ፣ በቤተሰባችን ላይ ታላቅ ዋጋ መስጠት አለብን። እራትን ከቤተሰብ ጋር አብሮ እንደመብላትና በቤተሰብ የቤት ምሽት በመሳተፍ እንዲሁም አብሮ ጥሩ ጊዜ በማሳለፍ አይነት ቀላል ነገሮችን አብሮ በማድረግ ጥልቅና አፍቃሪ የቤተሰብ ግንኙነቶችን ለመግንባት እንችላለን። በቤተሰብ ግንኙነት *ፍቅር* ማለት *ጊዜ* አብሮ ማሳለፍም ነው። እርስ በራስ ጊዜን መስጠት ለቤት ውስጥ ስምምነት የመገኘት ዋና ቁልፍ ነው። ስለእርስ በራስ ወሬ ማውራት ሳይሆን፣ እርስ በራስ እንነጋገራለን። እርስ በራስም እንማራለን፣ እናም አንድነታችንና ልዩነታችንንም እናከብራለን። ወደ እግዚአብሔርም በቤተሰብ ጸሎት፣ በወንጌል ጥናት፣ እና በሰንበት አምልኮት ስንቀርብም፣ እርስ በራስ መለኮታዊ ግንኙነት እንመሰርታለን።

ያለን ሶስተኛው ዋና ግንኙነት ከሌሎች ሰዎች ጋር ነው። ይህን ግንኙነት አንድ ሰው ከሌላ ጋር ስለሌሎች ፍላጎቶች ስሜት በማኖር፣ በማገልገል፣ እናም ጊዜአችንን እና ችሎታችንን በመስጠት እንገነባለን። በእድሜና በበሽታ ፈተናዎች የተቸገሩ ቢሆኑም ግን ብዙም ለማድረግ ባይችሉም ለማደመጥ ውሳኔ ባደረጉ አንድ እህት በጣም ተደንቄ ነበር። ስለዚህ በእያንዳንዱ ሳምንት የተቸገሩ ወይም የሚሰቃዩ ሰዎችን ይመለከቱና ከእነርሱ ጋ ጊዜ ያሳልፋሉም ያደምጣሉም። በብዙ ሰዎች ህይወት ላይ ምን አይነት በረከት ነበረች።

አራተኛው ዋና ግንኙነት ከእራሳችን ጋር ነው። ከራሳችን ጋር ግንኙነት መኖሩ ልዩ የሆነ ቢመስልም፣ ግንኙነት አለን። አንዳንድ ሰዎች ከእራሳቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት የላቸውም። እራሳቸውን እስከሚጠሉ ድረስ እራሳቸውን ይወቅሳሉ እናም እራሳቸውን አሳንሰው ይመለከታሉ። ቀስ እንድትሉና ትንሽ ጊዜ እራሳችሁን ለማወቅ እንድታሳልፉ ምክር እሰጣችኋለሁ። ተፈጥሮን ለመመልከት ሂዱ፣ የጸሀይ መውጣትን ተመልከቱ፣ የእግዚአብሔር ፍጥረት ተደሰቱባቸው፣ ደግም የተመለሰውን ወንጌል እውነቶች አስላስሉ፣ እናም ለእናንተ ምን ትርጉም እንደላቸው እወቁ። እናንተን የሰማይ አባት እንደሚመለከታችሁ መለኮታዊ ችሎታ እንደላቸው ውድ ሴት ወይም ውድ ወንድ ልጆቹ እራሳችሁን ለመመልከት ተማሩ።

## በንጹህ ወንጌል ተደሰቱ

ወንድሞችና እህቶች፣ ጥበብ ይኑረን። ወደ ደግም ወደተመለሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ንጹህ የወንጌል ትምህርት ውህ እንመለስ። በቀላልነታቸው እና በግልፅነታቸው በደስታ ተካፈሉ። ሰማያት እንደገና ተከፍተዋል። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እንደገና በምድር ላይ ነው፣ እናም የዚህም እውነት እና ብዛት ያለው የደስታ ምንጭ ነው።

ወንድሞችና እህቶች፣ የምንደሰትበት ታላቅ ምክንያት አለን። ህይወት እና በፍጥነት የሚኬድበት እና ብዙው ችግሮቹ ለመደሰት አስቸጋሪ አድርጎባችኋል፣ አሁንም ምናልባት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ በሆኑት ላይ ለማተኮር ጥሩ ጊዜ ነው።

ጥንካሬ የሚመጣው በመሯሯጥ ሳይሆን በእውነት እና በብርሀን ፅኑ መሰረት ላይ በመመስረት ነው። ይህም የሚመጣው ትኩረታችንን እና ጥረቶቻችንን ደግም በተመለሰው በኢየሱስ ክርስቶስ መንጌል መሰረታዊ ላይ በማሳረፍ ነው። የሚመጣውም ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ለሆኑት መለኮታዊ ነገሮች ትኩረት በመስጠት ነው።

ህይወታችንን ትንሽ ቀለል እናድርግ። ህይወታችንን በአድናቆት ቀላል በሆነው፣ ትርጉም፣ ደስታ እና ሰላም ወደለው ህይወት ወደሚመራው በክርስቲያን ደቀመዛሙርትነት ትሁት መንገድ ላይ ለማተኮር አስፈላጊ የሆኑትን ቅያሬዎች እናድርግ። በረከቴን ለእናንተ በመስጠት፣ ስለዚህ የምጸልየው በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ስም ነው፣ አሜን።

**ማስታወሻዎች**

1. ማህተመ ጋንዲ, በሌሪ ቻንግ, *Wisdom for the Soul* (2006), 356።
2. ዳለን ኤች. ኦክስ፣ "Good, Better, Best," *Liahona,* ህዳር 2007, 107።
3. ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ, በጆን ኩክ ውስጥ, comp., *The Book of Positive Quotations,* 2nd ed. (1993), 262።
4. ቪንስ ሎምባርዲ፣ በዶናልድ ቲ. ፊልፕስ ውስጥ፣ *Run to Win: Vince Lombardi on Coaching and Leadership* (2001)፣ 92።
5. ሉቃስ 18፥22።
6. 1 መሳፍንት 19፥12።
7. ሞዛያ 4፥27።
8. 2 ኔፊ 25፥26።
9. 1 ቆሮንቶስ 12፥31፤ ኤተር 12፥11።
10. ዮሀንስ 14፥6።
11. መዝሙር 46፥10።
12. ጄ ኢ. መኮሊክ፣ *Home: The Savior of Civilization* (1924), 42; ደግሞ Conference Report, ሚያዝያ 1935, 116ን ተመልከቱ።

© 2010 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩኤስኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/09 (እ.አ.አ)። ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/09 (እ.አ.አ)።
*Visiting Teaching Message, November 2010* ትርጉም። Amharic። 09371 506